# “እኛ… ጉግማንጉግ፣ የምንጠላለፍ ወዘተ…. ነን”?

መዝገቡ ሊበን፣ከሜነሶታ
Segel143@gmail.com

የሚነሶታው ፍኖተ ጥበብ ማዕከል ı0ኛ አመቱን ሲያከበር ከተጋበዙት ታዋቂዎች ውስጥ አርቲስት አለምጸሃይ ወዳጆ አንዷ ነበረች። መድረክ ላይ ያነበበችው “እኛ…ነን” ግጥሟ ቢያሳምመኝ“የማታ እንጀራ”ዋን ወዲያው ገዝቼ አነበብኩት። እናም ግጥሟን እንዲህ ተቸሁ።

“የጊዜ ፍጥነቱ” የሚለው ግጥሟ በስነ-ጽሁፍ “ግነት” የሚሉት ይመስለኛል። አለምጸሃይ ለልጇ ጡጦ ልታመጣ ጓዳ ገብታ ስትመለስ፣ ጡጦ የምትጠብቀው ልጇ ባንዴ አድጋ፣ የመኪና ቁልፍ ፍለጋ፣ ሳሎኑን በብርበራ ስታንጋጋ ደረሰችባት። አጭር ግን ደግሞ ግሩም ግጥም ነው። በጥቂት መስመሮች ውስጥ ብዙ ለማለት መቻል አንዱ የግጥምን ብቃት እና ርቅቀት ማሳያ ይመስለኛል። ስለዚህ “የጊዜ ፍጥነቱ” ግጥሟ፣ የተሳካለት ነው። ጊዜ  የማይታይ፣ የማይዳሰስ፣ የማይሸት… ወዘተ… በስሜት ህዋሳቶቻችን፣ ህልውናውን የማናረጋግጠው “አብስትራክት” እና ሰው “የፈጠረው” *(የጊዜ ክፍልፋዮቹን፣ ከማይክሮ ሰከንድ እስከ ምዕተ አለም ያለውን የጊዜ ቀመር ማለቴ ነው)* በመሆኑ፣ እንዲሁም ሁልጊዜ የማንኖረው እኛ እንጂ፣ “ጊዜ” ሁልጊዜም ያለ በመሆኑ፣ ፈጥነን እያለፍን ያለነው እኛ እንጂ “ጊዜ” አለመሆኑን ከማሳሰብ ጋር “የጊዜ ፍጥነቱ”ን አድንቄላታለሁ።

እናም አለምጸሃይ ምን ጊዜ “ከእቅፌ ፈልቅቀህ ልጄን ወሰድካት” ስትለን ጭንቀት እና ግርምቷ፣ ጊዜን ወይም ጊዜ ጠልፎ ስለወሰደባት ልጇ ሳይሆን ራሷን “ጊዜየን ምን ሰራሁበት?” አይነት ሙግት የሞገተችበት፤ በልጇ አስታክካ ራሷን የጠየቀችበት ይመስለኛል--“እድሜየን ምን ሰራሁበት?” በሚል።

አለምጸሃይ በልጅነት የገባችበትን ኪነ-ጥበብ ይኸው እስካሁን ዘልቃበታለች። መስራት የፈለገችውን አይነት ስራ እየሰራች መኖሯ፣ መንፈሳዊ ደስታ የሰጣት፣ ለውጤትም ያበቃት ይመስለኛል። ሆኖም ግን ዛሬም “እድሜየን ምን ሰራሁበት?” በሚል ራሷን እየጠየቀች ነው። ይህ ጤነኛ ጥያቄ ይመስለኛል።

ጥያቄዋን እኔ ብቻ ሳልሆን በርካቶች የሚመልሱላትም ይመስለኛል። አለምጸሃይ በኢትዮጵያ ኪነ-ጥበብ ውስጥ ትልቅ ስፍራ ያላት ሰው ነች። አገር-ቤት ብቻ ሳይሆን አሁንም በስደት የትም ለገባነው አበሾች ስራዎችዋን እያቀረበች ያለች፣ በተለይ ልጆቻችን የራሳቸው የጽሁፍ ቋንቋ፣ ስነ-ጽሁፍ እና ቲያትርም እንዳላቸው እያወቁ ማደጋቸው… ወዘተ መልካም ስራዎችዋ ናቸው። ግንሳ እነዚህ አስተዋፅኦዎቿ በ“ጮሌነት” እና “ዶግ-አመድ ለማድረግ” ተነሳስታ የሰራቻቸው ስራዎች ናቸው እንዴ? ወይስ እሷ “እኛ”ን አይደለችም?

ስለ መልካም ስራዎቿ ያነሳሁትን ያህል፣ ሁሌም ባነበብኩ በሰማሁ ቁጥር የሚያመኝን እና የሚያብከነክነኝን ጉዳይ፣ የአለምጸሃይን የራሷን ግጥም ተንተርሼ፣ አብዛኛውን የዚህ አይነት ስነ-ጽሁፍ ጸሃፊዎችን፣ እንዲያውም በጽሁፍም ብቻ ሳይሆን፣ በእለት እለት ገጠመኝ ጫዎታዎቻችን ሁሉ አብዛኛዎቻችን የምንታወቅበትን፣ ስለማንነታችን የምንናገረውን “አበሻ ምቀኛ ነው፣ አይተባበርም…” አይነት የጅምላ አፍራሽ ትችት መልሼ ልተች ነው።

የአለምጸሃይን “እኛ…..ነን” አይነት ጭብጥ ያላቸው ስነ-ጽሁፍ ስራዎች በሬዲዮ ስሰማ እዘጋዋለሁ። እያነበብኩ ከሆነም አጀማመሩን አይቼ ወዲያው አቆማለሁ። አለምጸሃይ ካሁን ቀደም ደጋግማ እንዳነበበችው (ስለምትወደው ይመስለኛል) ነግራን፣ በእውን (ላይቭ) መድረክ ላይ እያነበበችልን ያለውን የ“እኛ…..ነን” ግጥሟን  አንድ ሁለቱን መስመር ስታነብ ግጥሙ ቅኝቱን ይቀይራል እያልኩ ስጠብቅ፣… እየባሰበት … እውነት ለመናገር ሆዴን አመመኝ። እናም አቋርጬ ከመውጣት ውጭ ሌላ ምርጫ አልነበረኝም። ወጣሁ።

መውጣቴ እንደገና ቆጨኝ። ጥሎ ከመውጣት ይልቅ ለምን የተሰማኝን አልጽፈውም እና መወያያ አላደርገውም? የሚል ሃሳብ መጣልኝ። አሁን ዘግይቻለሁ--በስልኬ አለመቅዳቴ ቆጨኝ። … ሳይደግስ አይጣላም--“እኛ…..ነን”ን “የማታ እንጀራ” መጽሃፏ ውስጥ አገኘሁት። የ“እኛ… ነን” ግጥም ባጭሩ፣ በሁለቱ ቃላት መሃል ያለውን ክፍተት [ “….” (ዳሽ)]፣ መጥፎ ነገሮችን ሁሉ እየለቀሙ ማስገባት ነው። በየዳሹ የሚገባው (የሚሞላው) ደግሞ እያንዳንዱ ስንኝ ውስጥ አለ። እንዲህ፡-

“እኛ እኛን የበደልን ነን”፣ “እኛ እኛን ያቆሰልን ነን”“እኛ ከተግባር የራቅን ነን”፣ “እኛ ተውተፍትፈን የወደቅን  ነን”፣“እኛ የኛን ፋይል የሰረቅን ነን”፣ “እኛ ጉግማንጉግ ቀንድ አውጣ ነን”፣ “እኛ ዶግ-አመድ ለማድረግ ማንም የማይቀድመን ነን”፣“እኛ ወገን ገለን ጥለን ጨርሰን ያበቃን ነን”፣… ወዘተ። መቸስ ይህን ጸለምተኝነት (pessimism?) ሁሉንም ቁልቁል ልጻፈው ብል፣ አንድ ሙሉ ገጽ የሚበቃኝ አይመስለኝም። ጊዜውም የለኝም። እናም ይኸው ቀድቼ ለጥፌዋለሁ።


# እኛ . . . ነን!

አንዳንዶቻችን ነን . . . እኛን የበደልን . . . ለእኛው ያጎደልን . . .
ጥይት ድምፅ ሳይሰጥ . . . እኛን ያቆስልን . . . እኛን የገደልን
በወሬ ዘመቻ በአሉባልታ መረብ ዙርያውን ተከበን፣
በሰው ጥሎ ማለፍ በእኔ እበልጥ ተርበን፣
ተውተፍትፈን ወድቀን . . . ተጥለፍልፈን ደክመን
እኛው በእኛው አለቅን፣ እኛው በእኛው ታመን፤
አፍ ጠብቀን ውለን፣ አፍ ለማየት ብቻ ንጋት ሲናፍቀን፣
«ምን አሉ?»ን ስንደግም፣ ከተግባር እርቀን፣
ሳይገሉ እየሞትን ያለ ጥይት ወድቀን፣
ከጠረጴዛ ላይ ከውይይት ዓለም - ቃላት የበጨቅን፣
ከ«ምን አሉ?» መንደር ከወሬ መዝገብ ቤት - ፋይል የሰረቅን፣
ከጦር ሜዳ ሳንደርስ ከጀብዱ ሳንውል መንገድ የደረቅን፣
ክራባታችን ሥር የግል ወንበር አምሮት አንቀን የደበቅን፣
አንቱነት የጠማን በወገን ትከሻ መጫን የናፈቅን፤
በጉራ ገበያ ወዳጅ አሳፍረን ጠላት ያሞገስን፣
ክብር ተቀብለን ውርደት ያወረስን፣
የትውልድ ጉግ-ማንጉግ የዘመን ቀንድ አውጣ ቅፅል የተሰጠን፣
ብልጠት ዓይን አድርገን ሆዳችን የዋጠን፣
ጮሌነት ቀብተን አፋችን ቀልሞ አደባባይ ውለን፣
ነጠላ አፍቃሪዎች ክምሩን በትነን፤
አንድ ጥይት ሳይጮህ ጠላት ሳይሰነዝር ጠላት ሳያጠቃን
ወገን ገለን ጥለን ጨርሰን ያበቃን፤
ሌላው ሲሰበስብ እኛ ለመበተን እንተበትባለን፣
አንዱ የደከመበት ገና ሳያፈራ፣ ክህደት ተማምለን እንዋዋላለን፤
ድፍረት ዕውቀታችን ቃላችንም ሐሰት ክህደት ቀፍቃፊዎች፣
ጠላት ሳይሰነዝር ጠላት ሳያጠቃ እርስ በእርስ ጠፊዎች፤
ለተንኾ አንመች ለቀሪ ክንድ አንሰጥ ያለን ሁሉ ማውገዝ፣
ትከሻ እንደገፍ ወይ አንተባበር ወይ አንተጋገዝ፤
ልባችን ደም ሳይሆን ንቀት እየረጨ፣
በምን ያውቃል ታጥረን ማመስገን ማሞገስ በውስጣችን ጫጨ፤
አፍ አልበቃ ብሎን ጆሮአችንን ሁሉ አፍ ማድረግ ያማረን፣
ማን አህሎኝ ቤት አድገን ትዕቢት ያስተማረን፤
ሽቅብ አሽሟጣቾች ከእኔ በላይ ባዮች፣
ከጠላት የባሰን ወገንን አቁሳዮች፣
አንዳንዶቻችን ነን . . . እኛን የበደልን ለእኛው ያጎደልን . . .
ጥይት ድምፅ ሳይሰጥ እኛን ያቆሰልን . . . እኛን የገደልን . . .
በዕውቀት አንድ አንሁን . . . በዕድሜም አንድ አንሁን . . . በሀብት
አንድ አንሁን . . .

90

እንዴት እምነታችን ይነጣጠል አሁን?
ጠላት በወገን ጠላት በዳበረ ጠላት በበረታ፤
እንደደላው ዜጋ ለማን ሊበጅ ነው ጧት ማታ አሉባልታ?
አጋር መፍጠር የለም . . . ጀግና ማፍራት የለም . . . አቋም
መያዝ የለም፤
ተያይዞ መዘመር ጠላትን ማሳፈር ለእኛ አልተፈቀደም?
«ምን አሉ?» ነው እንጂ «ምን ባደርግ ይበጃል?» ማለት
አንለምድም፤
ችግር ማማጥ በቀር ዘዴን አንፈጥርም መፍትሔ አንወልድም፤
ማጥፋት ተክነናል ንቀት መርቀናል፤
ወግ ሰቅዞ ይዞ ወደ ላይ ይለናል፤
ማክበር አይወጣንም . . . ማድነቅ አያውቀንም . . .
ምሥጋና አይደማንም፤
ዶጋ-አመድ ለማድረግ ማንም አይቀድመንም ጠላት አያሻንም፤
አንዳንዶቻችን ነን . . . እኛን የበደልን . . . ለእኛው ያጎደልን . . .
ጥይት ድምፅ ሳይሰጥ እኛን ያቆሰልን . . . እኛን የገደልን።

91

እኔ የሚገርመኝ፣ እንዲህ ሁላችንም በጅምላ "ከተግባር የራቀ" ከሆንን፣ አንዱ ከሌላው የማይተማመን፣ አንዱ ለሌላው ምቀኛ መሆኑ ... ወዘተ እየተነገረን እንዴት ብለን ነው የምንቀራረበው? እንዴት ነው ቁጭ ብለን ተደማምጠን የምንወያየው?

አለምጸሃይ "እኔ እና አንተን.." ብቻ ሳይሆን፣ ራሷንም ጨምራ ነው የምትወቅሰው--"እኛ..." እያለች። እንዲያውም "አንዳንዶቻችን..." ይላል እና ጅምላ ውንጀላ አይደለም..." ብሎ የሚሞግተኝ እንደሚነሳ አውቃለሁ። ሆኖም ግን ኪነ-ጥበባችን፣ በኛ ወስተ ስላለነው "አንዳንዶቻችን" መጥፎዎች ከሚናገር፣ ስለ "አንዳንዶቹ" መልካም ሰብዕና ስላላቸው ሰዎች ቢያነሳ፣ የነዚህን "አንዳንድ" ሰዎችን መልካም ስራ የሚከተል ትውልድ ማፍራት የምንችል ይመስለኛል። እርስ በርስ ስለመጠላለፋችን፣ ስለምቀኝነታችን ወዘተ ደጋግሞ ማቅረብ የትም አያደርሰንም ብቻ ሳይሆን፣ እርስ በርስ እንዳንተማመን የሚያደርግ ይመስለኛል።

ደሞኮ ራሷም የታዘበችው በምልካም ስራቸው የሚመሰገኑ ሰዎች አሉን። አንዷ ራሷ ናት። በየአገሩ እየተጋበዘች የተወደሰችበት ነው። ዛሬም ይኸው የሚነሶታው "ፍኖተ ጥበብ"ን ነ0ኛ አመት በዓል ስኬት ይኸው ራሷ እየመሰከረችለት አይደል'ንዴ? ይኸው ታዋቂውን እና የአይነ-ስውሩን ሙዚቀኛ እና ድምጻዊው ተሾመ አሰግድን የህይወት ስኬታማነት፣ ለመጪው ትውልድ አርአያነት፣... እየተሸለመ... ራሷ እየነገረችን አይደል እንዴ? ምነው ስለ ደራሲ እና ጋዜጠኛ በዓሉ ግርማ ታላቅ ሰብዕና አንገጥምም? አንዘፍንም? የቅንጅት ዘመኑን ኢትዮጵያዊ ለምን አናነሳውም? እስክንድር ነጋን እና አንዷለምን ... ወዘተ ያህል ውብ ሰብዕና ያላቸው ዜጎቻችንን ለምን አናነሳቸውም? ለምን ስለነሱ አንገጥምም?

አለምጸሃይ "እኛ...ነን" ግጥሟን ከማንበቧ በፊት፣ "... ምዕራባዊያኑ ያደጉት፣ በኪነ-ጥበብ ሰውን እየቀየሩ ነው..." አይነት ንግግር አድርጋልን ነበር። እርግጥ ነው። ለአገር እድገት እና ልማት ኪነ-ጥበብ ሰውን በመቀየር አኳያ ያለው ፋይዳ ትልቅ

ነው። በየጊዜው የተፈራረቁብን አምባገነኖች፣ የመናገር እና የመጻፍ ነጻነታችንን በነፈጉን ቁጥር፣ ወደ ድህነት እና ባርነት ቁልቁለት እየገፉን እንደሆነ ከቶ አይገባቸውም። ቢገባቸውም ግድ የላቸውም።

አለምጸሃይ እንዳለችው፣ ኪነ-ጥበብ ሰውን በመቀየር አኳያ ያለው ፋይዳ ትልቅ ነው። ሆኖም ግን እንደ ኪነ-ጥበብ ስራው ጭብጥ፣ ቅርፅ እና ይዘት፣የሚያስከትለው ወጤትም ይለያያል። የ"እኛ ...ነን" አይነት ግጥም ግን ሰውን በአሉታዊ መልኩ የሚቀይር፣ እርስ በርስ እንድንፈራራ፣ እንዳንተማመን፣ እንድንጠራጠር... ወዘተ የሚያደርግ ነው። የሚገርመው ነገር፣ አብዛኛው ሰው እንዲህ "አበሻ አብሮ መብላት እንጂ አብሮ መስራት አይወድም"፣ "አበሻ ወትሮም ... መጠላለፍ... ነው"፣ ሲል፣ ራስን እና የሚነግረውን ሰው ከዚያ "ምቀኛ" እና እርስበርሱ "ተጠላላፊ" አበሻነት ራሱን አውጥቶ ነው። ሌላው ሰው እሱን ራሱን እንደዚያ እንደሚለው ግን ላፍታም የሚያስብ አይመስልም። ሁልጊዜ ምቀኛው እና "ጠላፊው" ሌላው አበሻ ነው።

ህዝብን በጅምላ (ጀነራላይዜሽን) መውቅስ የትም አያደርሰንም፣ እንደሚመስለኝ ከዚህ "አበሻ ምቀኛ ነው፣ አበሻን ማመን ድሮም... አበሻ አብሮ ሙብላት እንጂ መስራት አይሆንለትም ወዘተ..." ከሚል መውጫ-የለሽ አዙሪት (vicious circle) መውጣት ያለብን ይመስለኛል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ጀምሮ እጅግ በርካታ የድሮ ዘፈኖችን እየሰማሁ ነው። በትዝታ መልሰው መንፈሴን ያስደሰቱኝን ያህል፣ ስለምቀኝነታችን የተገጠሙ ግጥሞች እና የዘመሩ አርቲስቶች ቁጥራቸው ቀላል አይደለም።

> "ያለም ሳይንቲስቶች ብዙ ነገር ሲሰሩ፤
>
> ምነው ለምቀኝነት መድሃኒት አልፈጠሩ"

አይነት ግጥም አንዱ ነው።

እንዲህ አይነት የስነ-ጥበብ ስራዎችን አለማበረታታት ያለብን ይመስለኛል። እንደማህበረሰብ አባልነቴ ሁሉም አበሻ "ምቀኛ... እርስ በርሱ የሚጠላለፍ..." ነው የሚል እምነት የለኝም። እንዲያው "ነው" ቢባልም እንኳን፣ "አበሻ ምቀኛ ነው" እያሉ ምቀኝነትን ማጥፋት የሚቻል አይመስለኝም። እንዲያውም ያባብሰው ይመስለኛል።

"... ኢጋር መፍጠር የለም፣ ጀግና መፍጠር የለም... አቋም መያዝ የለም..." በማለት ኢጋር፣ ጀግና መፍጠር፣ አቋም መያዝም አይቻልም። በዓሉ ግርማን ያህል ታላቅ ሰው አለን። አንዱን የግጥም ምሽት "የበዓሉ የስነ-ግጥም ምሽት" ብሎ መሰየም፣ አንዷለምን የመሰለ መሪ ተፈጥሯል፤ በግፍ እየማቀቀ አለ። በግጥም ምሽት እናስበው። "የእስክንድር ነጋ ጽሁፎች ምሽት" ብሎ በስሙ አንዲት ሰአት በመወያየት ስሙን ማጉላት እና ማውጣት ሌላ እስክንደር መፍጠር ያስችላል። በቀለ ገርባ ሌላው ለህሊናው የሚኖር ምሁር ነው። እነዚህ ግሩም ሰብዕና ያላቸው ጀግና ዜጎቻችን ናቸው። እንዲያው በጅምላ፣ ጀግና መፍጠር የማይችል አገር እና ህዝብ አድርጎ መሳል፣ ጀግና አያስፈጥርም።

ጽሁፎ ውይይት ቢቀሰቅስ እና ጉልበት ቢያገኝ ብዬ በጉልበተኛ (ታዋቂ ማለቴ ነው) ሰው ትችቴን ጀመርኩ እንጂ፣ ይኼ ችግር የሷ ብቻ ሳይሆን፣ ራሴን ጨምሮ ያብዛኛዎቻችን ችግር ይመስለኛል።

የአዲሲቷ ኢትዮጵያ የትብብር ንቅናቄ (SMNE) መስራች አቶ ኦባንግ ሜቶ በድረ-ገጻቸው በቅርቡ "Harmonious society starts by talking to each other, rather than about each other." በማለት ያወጡትን አባባል ለኔ እንደተናገሩልኝ እቆጥረዋለሁ።

ሰገል ጋዜጣ፣ ከሚነሶታ!